በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ለማሰስ እየሞከሩ ነው?

OFFICE OF THE STUDENT ADVOCATE



# የወላጅ እና ቤተሰብ ሁለገብ መመሪያ


መጨረሻ የዘመነው፡ ዲሴምበር 2022

መርዳት እንችላለን። እዚህ ይጀምሩ።

የተማሪዎች ተከራካሪ ቢሮው ሁሉም ቤተሰቦች በዲስትሪክቱ ውስጥ የሕዝብ ትምህርትን መዳሰስ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። እውቀት እና ተደራሽነት በዘር፣ በኢኮኖሚ ደረጃ፣ በቋንቋ ወይም ተንቀሳቃሽነት ላይ የተገደቡ ወይም የተወሰኑ መሆን የለባቸውም።

የወላጅ እና ቤተሰብ ሁለገብ መመሪያችን ቀደም ሲል በተናጠል በድረ ገጻችን ላይ የቀረቡ እና በአካባቢያዊ ዝግጅቶች ላይ የታተሙ ወላጅን ማዕከል ያደረጉ ሰነዶች ስብስብ ነው። የሚከተሉት የመርጃ ሀብቶች ስብስብ የተነደፉት በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ስርዓትን መዳሰስ ላይ ቤተሰቦችን ለመርዳት ነው። በልጅዎ ትምህርት ቤት ፖሊሲዎች እና አካሄዶች ላይ ካለ ጥልቅ ግንዛቤ ጋር ሲጣመሩ አንዳንዶቹ መሳሪያዎች በጣም ጠቃሚ ናቸው።

እነዚህን የመርጃ ሀብቶች በአንድ መመሪያ ውስጥ በማስቀመጥ፣ በዲሲ ያሉ ወላጆች እና ቤተሰቦች የማወቅ መብት ያላቸውን መረጃዎች በአንድ ምቹ ሰነድ ውስጥ ማግኘት ይችላሉ።



Dan Davis
ዋና የተማሪዎች ተከራካሪ

ስልክ ቁጥር፦ (202) 741-4692
ኢሜይል፡ student.advocate@dc.gov
የድር ጣቢያ አድራሻ፡ studentadvocate.dc.gov
441 4th Street NW 723N, Washington, DC 20001

# የወላጅ እና ቤተሰብ ሁለገብ መመሪያ


**የሕዝብ ትምህርት በዲሲ**
ገጽ 2

**ውጤታማነት/ፈተና**
ገጽ 5

- የማወቅ መብት፡ ስኬት
- የማወቅ መብት፡ የPARCC ውጤቶች
- ወደ ምረቃ የሚወስደው መንገድ
- አማራጭ መንገዶች

**ባሕርይ**
ገጽ 9

- የማወቅ መብት፡ ባህሪ
- ጉልበተኝነት
- የጉልበተኝነት ምርመራ ሂደት
- የአእምሮ ጤና መርጃዎች
- የማወቅ መብት፡ የዲሲፕሊን ፖሊሲዎች
- የማወቅ መብት፡ የዲሲፕሊን ህግ

**የትምህርት ክትትል**
ገጽ 15

- የማወቅ መብት፡ መገኘት
- የማወቅ መብት፡ አርፈድነት
- የማወቅ መብት፡ አለመኖር

**ምዝገባ**
ገጽ 18

- የማወቅ መብት፡- ምዝገባ
- የማወቅ መብት፡ Pre-K3/Pre-K4
- የማወቅ መብት፡ ቤት እጦት።
- የቤት እጦት ምንጭ ኪት
- የማወቅ መብት፡ ወታደራዊ ቤተሰቦች


**የልዩ ፍላጎት ትምህርት**
ገጽ23

- የማወቅ መብት፡ ልዩ ትምህርት
- የፌዴራል ልዩ ትምህርት ሕግ
- የዲሲ ልዩ ትምህርት የመሬት ገጽታ
- የግለሰብ የትምህርት እቅድ (IEP) v 504
- የልጅ ፍለጋ እና የሂደት ጥበቃዎች
- የማወቅ መብት፡ ለጣልቃ ገብነት ምላሽ መስጠት

**ተጨማሪ መርጃ ሀብቶች**
ገጽ 29

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ከ 60 በላይ የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEAs) ወይም የተናጠል የ ትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች አሉን። የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) እና እያንዳንዱ የተናጠል የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት አውታረ መረቦች የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ናቸው።

## በዲሲ ያሉ ትምህርት ቤቶች እንዴት ነው የሚሰሩት




የልጅዎ የሕዝብ ትምህርት ቤት የራሱ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅሮች፣ ፖሊሲዎች እና አካሄዶች ያሉት LEA አለው - ሁሉም በየራሳቸው ድር ጣቢያ ላይ ሊገኙ ይችላሉ።

**የትምህርት ምክትል ከንቲባ**: https://dme.dc.gov
**የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ**: https://osse.dc.gov
**የዲሲ ካውንስል**: https://dccouncil.us/council
**የስቴቱ የትምህርት ቦርድ**: https://sboe.dc.gov
**ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች**: https://dcps.dc.gov
**የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች አውታረ መረቦች**: https://www.dcpcsb.org/find-a-school

በዲሲ ውስጥ ስላለው የሕዝብ ትምህርት አወቃቀር የበለጠ መረጃ በድረ ገጻችን በ studentadvocate.dc.gov በ Informational & Advocacy Resources and Tools (የመረጃ እና የተከራካሪ መርጃዎች እና መሳሪያዎች) ትር ስር ይገኛል ።)

# ሊያውቋቸው የሚገቡ ቃላት

**DME፣ የትምህርት ምክትል ከንቲባ**
የከንቲባው የአካዳሚክ ምርጥ ልምድን ለማሳደግ እና ተግባራዊ ለማድረግ የድስትሪክት አቀፍ የትምህርት ስልትን ይቆጣጠራል, የመስተጋብሮችና የመስቀለኛ መዋቅሮችን ማስተባበር ይቆጣጠራል; ለትምህርት ተያያዥ ኤጀንሲዎች የበላይ ሀላፊ ይሰጣል

**OSSE፣ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ**
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት (ዲሲ) ኦፊሴላዊ የስቴቱ የትምህርት ኤጀንሲ፤ በትምህርት ነክ ጉዳዮች ላይ ለ LEAs እና ለወላጆች መረጃን፣ የፖሊሲ መመሪያዎችን እና ሀብቶችን ያቀርባል

**SBOE፣ የስቴቱ የትምህርት ቦርድ**
ለስቴቱ የትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ ምክር ይሰጣል፣ በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በስቴት-ደረጃ ያሉ ፖሊሲዎችን ያጸድቃል

**LEA፣የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ**
የሕዝብ አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን የሚያንቀሳቀስ ሕጋዊ አካል፤ DCPS የራሱ LEA ነው እንዲሁም እያንዳንዱ ቻርተር አውታር የራሱ LEA ነው፤ እያንዳንዱ LEA የራሱ የሆኑ የፖሊሲዎች ስብስቦችን ይፈጥራል እንዲሁም የፌዴራል እና የስቴት ፖሊሲዎችን ተግባራዊነት ይቆጣጠራል

**DCPS፣ ዲሲ የህዝብ ት/ቤቶች**
በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የተለመደው የትምህርት ቤት ስርዓት፤ ማዕከላዊ ባለስልጣን የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ቻንስለር ነው

**ከመማሪያ ክልል ውጪ**
በ DCPS ውስጥ የመማር መብት ያለበት ትምህርት ቤት ሳይሆን፤ ከተማሪው የመኖሪያ አካባቢ ወሰን ውጭ ያሉ ትምህርት ቤቶች

# ሊያውቋቸው የሚገቡ ቃላት

**ከመማሪያ ክልል ውጪ**
በ DCPS ውስጥ የመማር መብት ያለበት ትምህርት ቤት ሳይሆን፤ ከተማሪው የመኖሪያ  አካባቢ ወሰን ውጭ ያሉ ትምህርት ቤቶች

**የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ (PCSB)**
በዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን ላይ ሥልጣን አለው፣ ከአጠቃላዩ የማመልከቻ ሂደት  በኋላ፤ PCSB ለሚያዛቸው ት/ቤቶች ቁጥጥር እና ድጋፍ ይሰጣል

**የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች (PCS)**
በ PCSB በጸደቁ ስምምነቶች ስር ከክፍያ ነፃ፣ ገለልተኛ የሆኑ ትምህርት ቤቶች፤ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት በሆነ ሰፈር ለሚገኙ ተማሪዎች የመብት -ጉዳይ ትምህርት ቤት አይደለም፤ በሎተሪ አማካኝነት ማመልከት ያስፈልገዋል

**የሎተሪ እጣ**
ተማሪዎች በክልል በሚገኙ ተሳታፊ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ ከመኖሪያ ክልል  ውጪ DCPS፣ የ DCPS ቅድመ-መዋዕለ-ሕጻናት ፕሮግራሞች እና የ DCPS ከተማ-ዓቀፍ  መራጭ ትምህርት ቤቶች በነጠላ ነሲብዊ እጣ አማካይነት ለመግባት የሚያስችላቸው ሒደት

**My School DC**
ተሳታፊ ለሆኑ ትምህርት ቤቶች የሎተሪ ዕጣ አሰራርን ያስተዳድራል፤ ተሳታፊ ያልሆኑ  ቻርተር ትምህርት ቤቶች የራሳቸው የሎተሪ ሂደት አላቸው፤ ማዛመዶች  በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በሚገኙ ቦታዎች ቁጥር ላይ የተመሰረቱ ናቸው

### ውጤታማነትን

# የማወቅ መብት



- ልጄ ወደ ቤት በሚያመጣው ጽሑፍ የተፈተነ ይመስላል?
- ልጄ እንዴት የበለጠ እንደሚማር አውቃለሁን? ልጄ ስኬታማ እንዲሆን በቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላለሁ?
- ልጄ ለመዝናናት እንዲያነብ ማድረግ የምችለውን ሁሉ እያደረግሁ ነው?
- ስለ ምረቃ እና መደበኛ ምዘናዎች ትምህርት ቤቱ ለእኔ ምን ያህል መርጃ ሀብቶች እንዳለው አውቃለሁ
- በልጄ ዙሪያ ስለ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት አሳያለሁ?
- ለልጄ የክፍል ደረጃ ያሉትን የስቴት መስፈርቶች ጥናት አድርጌያለሁ? ልጄ በቤት ውስጥ መስፈርቶችን ጠንቅቆ እንዲያውቅ እየረዳሁት ነው?
- ልጄ ተጨማሪ እገዛ ካስፈለገው የአካዳሚክ አገልግሎቶችን ጠይቄያለሁ/ፈልጌያለሁ?
- በቤት ውስጥ፣ የልጄን ማህበራዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ግልጽ ፍላጎቶች፣ ሀላፊነቶች እና ውጤቶች አሉኝ?
- ከልጄ አስተማሪዎች ጋር ሽርክናን ገንብቻለሁ? ከነሱ ጋር እንዴት መግባባት እችላለሁ?

የሚከተሉት ጥያቄዎች የተማሪን ውጤታማነት በሚመለከቱበት ወቅት አጋዥ ውይይት መጀመርያ ናቸው።



- ልጄ በክፍል ደረጃው ወይም ከዚያ በላይ እየሰራ ነው?
- በተለምዶ የልጄን የግል ፍላጎቶች ለማሟላት ትምህርቱን እንዴት ትለያያላቹ?
- በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የትምህርት ክንውን ክፍተት አለ?
- ለልጄ የክፍል ደረጃ ያሉት የምረቃ/የመዛወሪያ መስፈርቶች ምንድ ናቸው? የሚፈለጉ መደበኛ መመዘኛዎች አሉ?
- ልጆች እንዴት በተሻለ መንገድ እንደሚማሩ የት/ቤቱ ፍልስፍና ምንድን ነው?
- በዚህ የትምህርት ምእራፍ ውስጥ ምን አይነት ደረጃዎችን ነው የምትመዝኑት?
- ጥሩ ምሳሌ ምን እንደሚመስል ልጄ አውቆ ይገነዘባል?
- የልጄን ማህበራዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሊኖሩኝ የሚያስፈልጉት መዋቅሮች ምን ምን ናቸው? እሱ ወይም እሷ ከእኩዮቻቸው ጋር እንዴት ምላሽ ይሰጣሉ?
- በልጄ ትምህርት ቤት ውስጥ በፈቃደኝነት ለመሥራት ምን ምን እድሎች አሉ? የልጄን መሻሻል በተመለከተ እናንተን ለማግኘት ለኔ ምርጡ መንገድ ምንድነው?

ውጤታማነትን

# የ PARCC ነጥቦች

የ PARCC ውጤቶች ሲተረጉሙ የሚከተሉት ጠቃሚ ምክሮች አጋዥ ናቸው።

PARCC ተማሪዎች በሂሳብ እና በእንግሊዝኛ በክፍል ደረጃ ምን ያህል እንደተማሩ ለመለካት የተዘጋጀ ብሄራዊ መደበኛ ምዘና ነው።

| 650 ደረጃ 1 | 700 ደረጃ 2 | 725 ደረጃ 3 | 750 ደረጃ 4 | 805 ደረጃ 5 850 |
|---|---|---|---|---|

ተማሪው በክፍል-ደረጃ የሚጠበቅበት ላይ ለመድረስ ተጨማሪ ድጋፍ ሊያስፈልገው ይችላል።

ተማሪው በክፍል-ደረጃ የሚጠበቁበትን ያሟላ ሲሆን ለቀጣዩ ክፍል ዝግጁ ነው።

- ለእንግሊዝኛ እና ለሂሳብ፣ አንድ ተማሪ በ 650 እና በ 850 መካከል አጠቃላይ ነጥብ ይሰጠዋል።
- አጠቃላይ የነጥብ መጠን፣ 650 - 850፣በአምስት ደረጃዎች ይከፈላል።
- አጠቃላይ ነጥቡ ከላይ እንደሚታየው አሞሌ አይነት ከነጥብ ( 742 ) ጋር በመቀመጥ በቀስት ተደርጎ ብዙ ጊዜ ይታያል።

**ደረጃ 5:** ከሚጠበቀው በላይ ሆኗል

**ደረጃ 4:** የተጠበቀውን ያህል ሆኗል

**ደረጃ 3:** ወደሚጠበቀው ያህል ተቃርቧል

**ደረጃ 2:** በግማሽ የሚጠበቀውን ያህል ሆኗል

**ደረጃ 1:** እስካሁን የሚጠበቀውን ያህል አላሟላም

## እንግሊዝኛ

ንባብ (ከ10-90 መካከል ነጥብ ተሰጥቷቸዋል) — የተወሰኑ ክህሎቶች

መጻፍ (ከ10-60 መካከል ነጥብ ተሰጥቷቸዋል) — የተወሰኑ ክህሎቶች

## ሒሳብ

- ዋና ይዘት
- ተጨማሪ እና ደጋፊ ይዘት
- ሒሳባዊ ምክንያታዊነትን መግለጽ
- ሞዴሊንግ እና አተገባበሩ

የተወሰኑ ክህሎቶች

ሁለት ዋና ዋና ንዑስ ምድቦች አሉ፡ ንባብ እና ጽሁፍ። እያንዳንዱ ንዑስ መደብ (ቁጥር በመጠቀም) ነጥብ የተሰጠው እንዲሁም ወደ ተወሰኑ ክህሎቶች ይከፈላል። የተወሰኑ ክህሎቶቹ ምልክቶችን በመጠቀም ነጥብ ይሰጣቸዋል።

ሒሳብ በተወሰኑ ክህሎቶች ይከፈላል (ለሂሳብ ምንም ንዑስ ምድቦች የሉም)። እነዚያ የተወሰኑ ክህሎቶች ምልክቶችን በመጠቀም ነጥብ ይሰጣቸዋል።

## ለተወሰኑ ክህሎቶች የሚውሉ ምልክቶች

↑ በክፍል ደረጃ ከሚጠበቁት በላይ

↔ ከክፍል ደረጃዎች የሚጠበቁትን ያሟላል ማለት ይቻላል

↓ በክፍል ደረጃ ከሚጠበቁት በታች

ለበለጠ መረጃ፣ https://osse.dc.gov/parcc ን ይጎብኙ።

# የመመረቂያ ጎዳና

## ኮርሶች እና መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1. ለመመረቅ ሁሉም ተማሪዎች 24 ካሪኒጂ ነጥቦችን [[Carnegie Units (Cus)] መጨረሽ አለባቸው:

- **ሒሳብ (Mathematics) (4.0)**

  ቢያንስ ቢያንስ አልጅብራ (Algebra) 1፣ ጂኦሜትሪ (Geometry)፣ እና አልጅብራ (Algebra) II ማካተት አለባቸው

- **ሳይንስ (Science) (4.0)**

  ሦስት የላብራቶሪ ሳይንሶችን ማካተተ አለበት

- **ማህበራዊ ጥናቶች (Social Studies) (4.0)**

  የዓለም ታሪክ (World History) 1 እና 2፣ የዩናይትድ ስቴትስ (United States) ታሪክ፦የዩናይትድ ስቴት መንግስት (United States Government)፣ እና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት (District of Columbia) ታሪክ ማካተት አለበት

- እንግሊዘኛ (English) (4.0)
- የዓለም ቋንቋ (World Language) (2.0)
- አርት (Art) (0.5)
- ሙዚቃ (Music) (0.5)
- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት (Physical Education/Health) (1.5)
- **ተመራጮች** (Electives) (3.5)

*ከአከባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA) ወይም ከሌላ ግዛት ውስጥ ከሚገኝ ትምህርት ቤት የተዘዋወሩ እንደሆነ፣ የትኛው ክፍል ላይ መዘዋወር እንዳለብዎ መጠየቅዎን አይርሱ።

*ተመራጭ (selective) ወይም የከተማ አቀፍ (citywide) ትምህርት ቤቶች ላይ የተማሩ እንደሆነ ለመመረቅ አንዳንድ ተጨማሪ ትምህርቶችን ሊወስዱ ይችላሉ።

2. ለመመረቅ ሁሉም ተማሪዎች 100 ሰዓት የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት አለባቸው።

## የውጤት ቅራኔ (Grade Disputation)

1. ስለ አመጡት የትምህርት ውጤት ከመምህርዎ ጋር ለመነጋገር ይሞክሩ።
2. ከትምህርት ርዕሰ መምህር ጋር ሕጋዊ የትምህርት ውጤት የይግባኝ ጥያቄ/ቅሬታ ያስገቡ። በደንብ ግልጽ ለሆኑ መመሪያዎች ከትምህርት ቤት አማካሪዎ/የትምህርት ቤት መመሪያ መጽሐፍዎን ይመልከቱ።
3. የመጨረሻ የይገባኛል ጥያቄዎን ለአካባቢው ትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ቦርድ ወይም ለኮሎምቢያ ዲስትሪክ የሕዝብ ትምህርት ቤት (DCPS) ዋና ተቆጣጣሪ ጋር ያስገቡ።

*ያለምክንያት ከትምህርት ገበታ መቅረት በዚያ ትምህርት የውጤት ቅነሳ ሊያስከትል ይችላል።

## የክሬድት ማስመለስ (Credit Recovery)

አንድ ተማሪ በትምህርቱ ከወደቀ ትምህርት ቤትዎ ክሬዲት የሚያገኙባቸውን ሌሎች አማራጮችን ሊያቀርብ ይችላል።

ታዋቂ አማራጮች

- ከመደበኛ ትምህርት ጊዜ በኋላ የሚሰጡ የማካካሻ ትምህርቶች
- የደንገዝገዝ (የማታ) ትምህርቶች
- የበጋ ትምህርት
- ተለዋጭ ቅንብሮች (alternative settings)

* ለእርስዎ ያሉትን አማራጮች እና በእርስዎ ትራንስክሪፕት ላይ ላይ እንዴት እንደሚመዘገቡ ለማወቅ ትምህርት ቤትዎን ይጠይቁ።

# የትኛው መንገድ ነው ምርጥ?

OFFICE OF THE STUDENT ADVOCATE

### የግዛቱ ዲፕሎማ ከጂኢዲ (GED)

ጂኢዲ (GED) ሰርተፊኬት ነው፣ ዲፕሎማ አይደለም።
የግዛቱን ዲፕሎማ የሚያገኙት በእርስዎ ጂኢዲ (GED) ውጤት ላይ የተመሰረተ ነው።

### የመጀመሪያ ቅደም ተከተል

- ለመመረቅ ምን ያህል ክሬዲት እንደሚያስፈልግዎ ይወቁ?
- ዕድሜዎ ከ 16 ዓመት በላይ ነው?
- በእርስዎ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰው ሌላ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም ላይ ስለመግባት ከእርስዎ ጋር ተማክሯል?

### ስለ እርስዎ ሁኔታ እውነቱ

ሕይወት ይከሰታል። በአብዛኛው ዕቅዶችመቀየር ይኖርባቸዋል። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዴት እንደሚጨርሱ የሚወሱኑት ውሳኔ ነው!

### ተማሪዎች የሚገጥሟቸው ፈተናዎች

- እርግዝና
- የቋንቋ/የኢሚግሬሽን መሰናክሎች
- የፍትሕ ስርዓት ጋር መገናኘት
- ጎዳና ተዳዳሪነት

### በእኔ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ መጨረስ አማራጭ ነው?

አዎ፣ የአይኢፒ [[(ልዩ ትምህርት) IEP] ያለዎት እንደሆነ በተለመደው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ዲፕሎማ ለማግኘት እስከ 22ኛ የልደት በዓልዎ ድረስ ጊዜ አለዎት፥

አዎ፣ ትምህርት ቤትዎ የደንገዝገዝ ክፍል ወይም የማታ ትምህርት የመሳሰሉ የክሬድት ማግኛ መርሀግብሮችን የሚሰጥ ከሆነ፥

አይ፣ ዕድሜዎ 18 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ እና ከአንድ ዓመት ሙሉ በላይ ወደኋላ የቀሩ እንደሆነ፥

አይ፣ የጸባይ ችግር ወይም ከትምህርት ገበታ ላይ የመቅረት ችግሮች ያለዎት እንደሆነ።

### እውነታዎች እና ጥቅማጥቅሞች

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ለማግኘት ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ 24 ሰዓት ክሬዲት ማግኘት ያስፈልጎታል።
- አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአንድ ዓመት ውስጥ እስከ 6 ክሬዲቶች ድረስ ያገኛሉ።
- ነፃ እና ተገቢ የሆነ ትምህርት የመማር መብት አለዎት።
- ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ በዲስትሪክት ኮሎምቢያ ውስጥ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲገቡ በሕግ ይገደዳሉ።

### የተለያዩ መርሀግብሮች (ፕሮግራሞች)

- አካዳሚ ኦፍ ሆፕ ፐብሊክ ቻርተር (Academy of Hope Public Charter)
- ባሉ ስተይ ከፍተኛ ደረጃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Ballou STAY Senior High School)
- ብሪያ ፐብሊክ ቻርተር (Briya Public Charter)
- ካርሎስ ሮዛሪዮ ፐብሊክ ቻርተር (Carlos Rosario Public Charter)
- ኮምዩኒቲ ኮሌጅ መሰናዶ (Community College Prep)
- ላይክ ኬሪየር አካዳሚ (LAYC Career Academy)
- ሉክ ሲ ሙር አካዳሚ (Luke C. Moore Academy)
- ማያ አንጀሎ ያንግ አደልት የመማሪያ ማዕከል (Maya Angelou Young Adult Learning Center) ሉክ ሲ ሙር አካዳሚ (Luke C. Moore Academy)
- ኔክስት ስቴፕ ፐብሊክ ቻርተር (Next Steps Public Charter)
- ሮዝቬልት ስቴይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Roosevelt STAY Senior High School)
- ዋሽንግተን ሜትሮፖሊቲያን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Washington Metropolitan High School)
- ዩዝ ቢዩልድ (Youth Build)

ከመሄድዎ በፊት፣ ያሉትን ተናባቢ ነገሮች እዚህ ላይ ይመልከቱ፥


- backontrack.osse.dc.gov
- https://dcps.dc.gov/page/opportunityacademy
- dcpcsb.org
- studentadvocate.dc.gov

ውጤታማነትን

# ባሕርይ


የሚከተሉት ጥያቄዎች የተማሪን ባህርይ በሚመለከቱበት ወቅት አጋዥ ውይይት መጀመርያ ናቸው።

## ራስዎን ይጠይቁ



- ልጄ በት/ቤት ወይም በአውቶቡስ ውስጥ ምን አይነት ባህርይ ማሳየት እንደሚጠበቅበት አውቃለሁ?
- ከልጄ ጋር ልነጋገርባቸው የሚገቡ ማናቸውንም የባህሪ ጉዳዮች አውቃለሁ? ልጄ በት/ቤት ወይም በአውቶቡስ ውስጥ ምን አይነት ባህርይ ማሳየት እንደሚጠበቅበት አውቃለሁ?
- በልጄ ትምህርት ቤት ውስጥ ስነ-ምግባርን በተመለከተ ያሉትን ፖሊሲዎች እና ደንቦች አንብቤያለሁ?
- ቤት ውስጥ የማውቃቸው ችግሮች ሲያጋጥሙኝ ከትምህርት ቤቱ ጋር እንዴት ልገናኝ እችላለሁ?
- የባህሪ ጥሰቶችን እና የሚያስከትሏቸውን ተያያዥ ውጤቶች አውቃለሁ?
- ልጄ ዓመፅ ተቀባይነት እንደሌለው ይገባዋል ወይ? የባህሪ ጥሰቶችን እና የሚያስከትሏቸውን ተያያዥ ውጤቶች አውቃለሁ?
- በቤት ውስጥ ባለ ባህሪ ላይ ያሉትን የትምህርት ቤት ፖሊሲዎች እና አካሄዶች እንዴት መደገፍ እችላለሁ?
- ቤት ውስጥ፣ የሚጠበቁ ነገሮች እና የሚከተሉ ውጤቶች አሉ?

## መምህርዎን ይጠይቁ



- ትምህርት ቤቱ ለልጄ ከባህሪው/ዋ አንጻር የሚጠበቀውን ሁኔታ እንዴት ይነግራል?
- ልጄ የባህርይ ችግር እንዳያጋጥመው ለመቆጣጠር/መከላከል እንድችል እንዴት ልትረዱኝ ትችላላችሁ? ትምህርት ቤቱ ለልጄ ከባህሪው/ዋ አንጻር የሚጠበቀውን ሁኔታ እንዴት ይነግራል? (ማንኛውም የባህሪ ችግር ከትምህርት ቤቱ ጋር ያጋሩ።)
- ልጄ እሱ/እሷ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ለማስወገድ ምን እንደሚያስፈልግ በእውነት ያውቃሉ እንዲሁም ይገነዘባሉ?
- ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ ባህሪ ያላቸው እና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ምን እየተደረገ ነው?
- የአዎንታዊ ባሕርይ ግንባታ እገዛ እና ድጋፍ ምንድናቸው (PBIS)?
- እንደ ወላጅነቴ፣ እኔ በቤት ውስጥ ልገነዘበው እና በስራ ላይ ላውላቸው የሚገቡ የሥነ ሥርዓት ፖሊሲዎች ምንድን ናቸው?
- ከናንተ ጋር ማጋራት ያለብኝን ነገሮች በተመለከተ ከትምህርት ቤቱ ጋር ለመነጋገር ምርጡ መንገድ ምንድነው? እንደ ወላጅነቴ፣ እኔ በቤት ውስጥ ልገነዘበው እና በስራ ላይ ላውላቸው የሚገቡ የሥነ ሥርዓት ፖሊሲዎች ምንድን ናቸው?
- የባህሪ እቅዳችሁን የምትመለከቱት እንደ ቀጪ ነው ወይስ እንደ አስታራቂ?
- ልጄ ታግዶ ከሆነ፣ ገለልተኛ የሆነ የይግባኝ ሂደት አለ? የይግባኝ ሂደቱ ምንን ያካትታል?

*ይህ መረጃ ከት/ቤትዎ መመሪያ መጽሀፍ ጋር ከተጣመረ ይበልጥ ጠቃሚ ነው።

# የጉልበተኝነትሬ ጣን ሉህ

## ማወቅ ያለብዎ ነገሮች

OFFICE OF THE STUDENT ADVOCATE

### 1 ጉልበተኝነት ምን ማለት ነው?

- ጉልበተኝነት የማይፈለግ፣ ተጠቂው ግልሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ጥለኛ ባህሪ ነው እና እውነተኛ ወይም በምናብ የሚታሰ የኋይል ሚዛን መዛባትን ያካትታል።

- ጉልበተኝነት ምናልባት እንደ ዘር፣ ፆታ፣ የመጡበት አገር፣ የቆዳ ቀለም፣ የወሲብ አዝማሚያ፣ የግል ገጽታ፣ የፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ ወይም የቤተሰብ የኑሮ ደረጃ የመሳሰሉ የተወሰኑ የግል ባህሪያት ላይ ሊመሰረት ይችላል ነገር ግን በዚህ ላይ ብቻ አይወሰንም።

### 2 የወጣቶች ጉልበተኝነት መከላከያ አዋጅ 2012

- በሕግ የታቀፈው ጁን 22 ቀን፣ 2012 ዓ.ም ላይ ነው።

- ሁሉም የዲሲ የሕዝብ እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች እንደዚሁም የዲሲ ኤጀንሲዎች ፖሊሲ ሊኖራቸው ይገባል።

- የወጣቶች ጉልበተኝነት መከላከያ ግብረሐይል (Youth Bullying Prevention Task Force) ተፈጥሯል፣ የሚያካትተውም የዲስትሪክቱ የመንግስት ኤጀንሲዎች፣ አስተማሪዎች፣ የት/ቤት አስተዳዳሪዎች፣ ወላጆች፣ የአዕመሮ ሕመም ስፔሻሊስቶች፣ እና ተጨማሪ ሰዎችን ነው።

### 3 የጉልበተኝነት አይነቶች

**የቃል**
ለምሳሌ ማፌዝ፣ የማይገባ ስም መስጠት፣ ማቅራራት

**አካላዊ፡**
ለምሳሌ መማታት፣ መራገጥ፣ መግፋት

**ማህበራዊ**
ለምሳሌ ሆን ብሎ አንድን ሰው ማግለል፣ ስለዛ ግለሰብ የሐሰት ወሬ ማሰራጨት

**ኤልክትሮኒክስ**
ለምሳሌ በጽሁፍ መልዕክት፣ በኢሜይል ወይም ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም የክፋት ወይም የማስፈራሪያ መልዕክት መላክ

### 4 የጉልበተኝነት መከላከያ ፖሊሲ

**ሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ የዲሲ ወጣቶችን- የሚያገለግሉ ኤጀንሲዎች እና ለትርፍ- ያልተቋቋሙ ድርጅቶች የጉልበተኝነት ፖሊሲ እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል።**

ይሄ የጎልበተኝነት መከላከያ ፖሊሲ የሚከተሉት ነገሮች ሊኖረው ይገባል፡ ትንታኔዎች፣ የሚያመጣው መዘዞች እና ተለዋዋጭነት፣ ሪፖርት ማቅረብ፣ ምርመራ እና የይግባኝ ጥያቄዎች።

ስለ የጉልበተኝነት መከላከያ ፖሊሲ የበለጠ መረጃ እዚህ ላይ ይገኛሉ፡

https://ohr.dc.gov/bullyingprevention/policy

### 5 ጠቃሚ ስልክ መደወያዎች

**ሁሉም ትምህርት ቤቶች ለዚህ ዓላማ የቆሙ ተወካይ ሰዎች አሏቸው።**

**የእርስዎ በዚህ ላይ ያግኙ፡**

https://ohr.dc.gov/page/knowyourpolicy

**ጠቃሚ ምክሮች፥**
Pr በጉልበተኞች እየተጠቁ ያሉ ልጆችን ወይም ሌሎችን የሚያጠቁ ጉልበተኛ የሆኑ ልጆችን ያግዟቸው፣ ምክንያቱም ሁለቱም አደገኛ እና ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ችግሮች ላይ ሊወድቁ ይችላሉ።

### 6 ጠቃሚ ግብዓቶች

**የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (Office of Human Rights) የጉልበተኝነት መከላከያ ገጽ ስለ ጉልበተኝነት መከላከያ አዋጅእና ስለ ጉልበተኝነት ፖሊሲዎች ጠቃሚ ግብዓቶች፣ ጠቃሚ ምክሮች እና ተጨማሪ መረጃዎች አሉት።**

ድረገጹን በዚህ አገናኝ ላይ ይጎብኙ
https://ohr.dc.gov/page/bullying prevention

ባሕርይ

# የማወቅመብት

# የጉልበተኝነት (ቡልዪንግ) ምርመራሂደት

ጉልበተኝነት (ቡልዪንግ) ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለወላጆችና ለቤተሰቦች ጭምር እንዲለዩ ሊያደርግ የሚችል ውስብስብ ጉዳይ ነው። የጉልበተኝነት ችግር ለመፍታትና ደህንነቱ የተጠበቀና አሳዳጊ የመማር አከባቢ ለመፍጠር ይመች ዘንድ ቤተሰቦች ሂደቱ እንዲገባቸው በማድረግ ለመርዳት ስለ ምርመራ ሂደት በተመለከተ ከታች ተጨማሪ ማብራሪያ አቅርበናል።

## የመጀመሪያምርመራ

የክስተቱየጽሑፍ ስነዳ በ2 ቀናት ውስጥ መደረግ ይኖርበታል፣ የሚከተለውንም ማካተት ይኖርበታል፡

1) በጉዳዩለተሳተፉ ተማሪዎች ተገቢ ከለላዎች ማካተት ይኖርበታል፣
2) ዒላማየሆነውንና ዒላማ የሆነው ቤተሰቦች ማሳወቅ ይኖርበታል፣
3) አነሳሹናየአነሳሹ ወላጅ ማሳወቅ ይኖርበታል።

## የተሰነደሪፖርት

የተሰነደሪፖርት በ30 ቀናት ውስጥ መደረግ ይኖርበታል፣ የሚከተሉትንም ማካተት ይኖርበታል፡ የክስተቱመግለጫ፣ የተሳታፊ ሰዎች ስሞች፣ ተደረገ የተባለው ክስተት የተፈጸመበት ቦታ፣ ጉልበተኝነት መፈጸሙንና አለመፈጸሙን፣ የተወሰደ እርምጃ

## የይግባኝሂደት

ምርመራውከተጠናቀቀ በኋላና ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ የመጨረሻ ውሳኔውን ዒላማውና አነሳሹ ይግባኝ የማለት መብት አላቸው። ይግባኞች በኦ.ኤች.አር. በኩል ሊደረግ ይችላል።

## ዒላማ

በምርመራጊዜ ትምህርት ቤቱ የልጁ ደህንነት ይረጋገጥ ዘንድ፣ እንዲሁም ደግሞ ለልጁ ደህና ነው ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ለወላጆች ለመንገር ምክኒያታዊ የሆኑ ጥረቶች ማድረግ ይኖርበታል። ልጁአይ.ኢ.ፒ. ያለው ከሆነ ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል። በሂደቱውስጥ ምስጢራዊነት መጠበቅ ይኖርበታል፣ ተማሪና ሞግዚትም የመጨረሻው ሪፖርት ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## አነሳሽ (ኢኒሼተር)

በምርመራጊዜ ትምህርት ቤቱ ምርመራው በተመለከተ ለአነሳሹ እንዲሁም ደግሞ ለልጁ ደህና ከሆነ ለወላጆች ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ልጁአይ.ኢ.ፒ. ያለውከሆነግምትውስጥመግባትይኖርበታል። በሂደቱውስጥምስጢራዊነትመጠበቅ ይኖርበታል፣ተማሪናሞግዚትምየመጨረሻውሪፖርትማግኘትይኖርባቸዋል።

## የትምህርትቤት መገናኛ አካል (ፖይንት ኦፍ ኮንታክት)

እያንዳንዱትምህርት ቤት ጉልበተኝነት በተመለከተ የሚያሳስቡ ነገሮች የሚያይ የጉልበተኝነት መከላከል መገናኛ አካል (ፖይንት ኦፍ ኮንታክት) አለው።

የርስዎንበ ohr.dc.gov ያግኙ።

### የማወቅመብት

# የአእምሮጤናሀብቶች

የአእምሮጤና እክል ላላቸው ልጆች በምንረዳበት ጊዜ የሚከተሉት አጋዥ ውይይት አስጀማሪጥያቄዎች ናቸው።

## የትምህርትቤት የአእምሮ ጤና ፕሮግራም

እያንዳንዱየህዝብና ቻርተር ትምህርት ቤት በዲፓርትመንት ኦፍ ቢሄቭየራል ሄልዝ (የባህርይ ጤና ዲፓርትመንት) የሚሰራ የአእምሮ ጤና ክሊኒሻን ያለበት ትምህርት-ቤት መሰረት ያደረገ ፕሮግራም አለው። ፕሮግራሙለወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው የመከላከል፣ የአስቀድሞ ጣልቃ ገብነትና የክሊኒክ አገልግሎቶች ያቀርባል። ትምህርትቤት መሰረት ያደረገ ካውንስለርዎ (አማካሪዎ) ለመለየት ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ። ለተጨማሪመረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ፡ https://dbh.dc.gov/service/school-behavioral-health-program

## ዲፓርትመንትኦፍቢሄቭየራልሄልዝ (የባህርይጤናዲፓርትመንት) የተደራሽነት የእርዳታ መስመር (አክሰስ ሄልፕላይን)

የተደራሽነት የእርዳታ መስመሩ (አክሰስ ሄልፕላይን) በባህርይ ጤና ሙያተኞች የሚሰራ ሲሆን ለ24/7 ያህል ለአገልግሎት ክፍት ነው። ሙያተኞችደዋዩን ለአስቸኳይ እርዳታ ወይም ለቀጣይ እንክብካቤ ሊመሩ ይችላሉ። አስቸኳይ የሳይክያትሪክ እንክብካቤ ለማግኘት፣ ችግር በመፍታት ረገድ እርዳታ ለማግኘት፣ ወይም ቀጣይ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ወይም ሌላ አይነት አገልግሎቶች መፈለግ አለመፈለግ ለመወሰን፣ እና/ወይም ሊገኙ የሚችሉ አገልግሎቶች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ወደ የተደራሽነት የእርዳታ መስመሩን (አክሰስ ሄልፕላይን) መደወል ይችላሉ። **1(888)7WE-HELP ወይም1-888-793-4357ይደውሉ**

## ማህበረሰብመሰረት ያደረጉ ድርጅቶች

የአእምሮጤና አገልግሎቶች ለዲስትሪክት ነዋሪዎች በማህበረሰብ መሰረት ያደረጉ በዲ.ቢ.ኤች. ፈቃድ ያላቸው (ሰርቲፋይድ) ድርጅቶች በኩል ይገኛሉ። አገልግሎቶቹየምርመራ ግምገማ (ዲያግኖስቲክ አሰስመንት)፣ መድህኒት፣ ምክር (ካውንስሊንግ)፣ እና የማህበረሰብ ድጋፍ ያካትታሉ። ነዋሪዎችበዲ.ቢ.ኤች. ድረገጽ ካለው ዝርዝር ወይም አቅራቢው ዘንድ በመደወል ወይም በመጎብኘት አገልግሎት አቅራቢን መምረጥ ይችላሉ። http://dbh.dc.gov/page/list-community-based-service-providers

## ቺልድረንስኤንድ አዶለሰንትስ ሞባይል ሳይክያትሪክ ሰርቪስስ (ቻምፕስ) (የልጆች እና ጎሮምሶች ተንቀሳቃሽ የአእምሮ ህክምና አገልግሎቶች)

ቻምፕስየአእምሮ ጤና ወይም የባህርይ ጤና ቀውስ ውስጥ ላሉ ልጆች፣ ወጣቶች (ቲንኤጀርስ)እና ጎረምሶችአስቸኳይ ምላሽ አገልግሎት የሚሰጥ ነው። ቻምፕስከዲ.ቢ.ኤች.፣ ከሎካል (የአከባቢ) ሆስፒታሎች፣ እና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት ጋር በአጋርነት ይሰራል፣ በዲስትሪክት ለሚኖሩ ልጆች እርዳታ ያቀርባል። ቻምፕስያለ ክፍያ፣ በዛኑ ቀን ወደ ትምህርት ቤት ይመጣል፣ 6-18 ዕድሜ ላላቸው ወይም እድሜያቸው እስከ 21 ለሆኑ በፎስተር (በሌላ ቤተሰብ ስር) ላሉ ወጣቶች ለ24/7 ይገኛል።
**(202) 481-1440** https://www.catholiccharitiesdc.org/champs/

የ ማወቅ መብት

# ሥነ ስርዓት ማስከበር ፖሊሲዎች

## መገንዘብ ያለብን ነገሮች

### ተገኝነት

የት፣ መቼ እና እንዴት ትምህርት ቤትዎ የሥነ ስርዓት ማስከበሪያ ፖሊሲዎችን እንዴት እንደሚያወጣ ዝግጁ እንደሚያደርግ ቁልፍ ነገር ነው። የአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ፖሊሲዎች በድረ ገጽ ላይ ብቻ ይለቀቃሉ ወይም በአመት አንድ ጊዜ ላይ ለወላጆች ታትመው ይሰጣሉ።

### ቅጣት የሚያመጡ ባህሪዎች

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚያስቀጡ የተለያዩ ባህሪያቶች ሊኖራቸው ይችላል። የቻርተር ትምህርት ቤቶች እያንዳንዱ የተለያዩ ጥቃቶችእንዴት ቅጣት መሰጠት እንዳለባቸው የየራሳቸው ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል። አንዳንድ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA) ጥቃቱን እና መዘዙን በዝርዝር የሚያስቀምጡ ሦስተኛ ወገኖች ላይ የሚመረኮዙ የሥነ ስርዓት ማስረከቢያ ፖሊሲዎች አሏቸው።

### መታገድ የውሂብ

እያንዳንዱ ዓመት ላይ፣ ኦሲ (OSSE) የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA) ሪፖርት የሚደረጉ እገዳዎችን እና ማባረሮች ቁጥር የሚያካትት የሥነ ስርዓት ሪፖርት ያወጣል።

ይሄ ሪፖርት እዚህ ላይ ይገኛል:

https://osse.dc.gov/page/discipline-report.

### አማራጭ ዝግጅቶች

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA) የክፍል ሥራዎችን እንዲያጠናቀቁ ለታገዱ ተማሪዎች ይፈቅዳል።

### የፍትህ ሂደት

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA)የፍትህ ሂደት መብቶችን ትርጉም አሰጣጣቸው ላይ ልዩነት አላቸው። ለምሳሌ፣ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ለሦስተኛ ወገን ይግባኝ እንዲጠይቁ ሊፈቅዱ ይችላሉ ሌሎች ደግሞ አይፈቅዱም።

## የማባረር የሥነ ስርዓት ማስከበሪያ ሂደት ላይ አማራጮች

### የስሜት ቁስልየሚያከሙ

ትምህርት ቤቶች የተማሪን የባህሪ መበላሸት ለመከላከልየስሜት ጤናን ያበረታታሉ።

### ፖሰቲብ ብሔቨር ኢንተርቬንሽንስ ኤንድ ሳፖርትስ (PBIS)

ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ባህሪ መበላሸት ለማገዝለግል የተዘጋጁ ዕቅዶችን ያዘጋጃሉ። ዕቅዶቹ የሚያካትቱት በተማሪው ፍላጎት እና የባህሪው መበላሸት የአደገኛነት ደረጃ መሰረት የሚደረጉ እርምጃዎችን ማካተት አለባቸው።

### የማስመለሻፍትህ አሰጣጥ

በተማሪው እና በተጠቂው/ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ ጤናማ ሁኔታ ለማስመለስ በሚደረግ ጥረት የማህበረሰብ ልምምድ በመጠቀም ተማሪዎች የራሳቸውን የባህሪ መበላሸት መለየት ይችላሉ። በአደጋ ላይ የሚገኙ የከፋ የቅጣት መዘዞች የሉም። ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የእነሱ ባህሪ መበላሸት በተጠቂዎች ላይ ያመጣውን ጉዳት እንዲማሩ ዕድሉን ይሰጣል። ትምህርት ቤቱ ጥቃት ባደረሰው እና በተጎጂው መካከል ውይይት እንዲደረግ ሁኔታውን ያመቻቻል። የወደፊት የባህሪ መበላሸትን ለመከላከል ትምህርት ቤቱ እርምጃዎችን ይወስዳል።

የ ማወቅ መብት

# የሥነ ስርዓት ማስከበር ሕግ

## የትምህርት የማሻሻያ ሕግ 2018 ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለተማሪዎች ማቅረብ*

ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ያሉ ተማሪዎችን እገዳ ይገድባል ሆኖም ግን አደገኛ የሆኑ ለደህንነት አስጊ ሁኔታዎች ላይ ይተገበራል በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ደግሞ ለሚፈጠሩ ጥቃቅን ግድፈቶች ላይ እንዳይተገበር ያግዳል። አንድተማሪ የታገደ ከሆነ፣ ይሄ ሕግ ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጪ እንዳሉ የመማር መብታቸውን ይጠብቃል እና ወደ ክፍሉ በተሳካ ሁኔታ እንዲመለስ ለተማሪው ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠይቃል።

*ከክፍል PK3-5 ድረስ ለትምህርት ዓመት18-19፣ ከክፍል 6-8 ድረስ ለትምህርት ዓመት19-20፣ እና ከክፍል 9-12 ድረስ ለትምህርት ዓመት 20-21 ላይ ይተገበራል።

### ትምህርት ቤቶች የሚችሉት...

- በባህሪያቸው የተነሳ ተማሪዎችን አለመጋበዝ
- በሥነ ስርዓት መጓደል የተነሳ ትምህርት በሚሰጥበት ቀኑን ሙሉ በጎ ባልሆነ ሁኔታ ማባረር
- ጥቃት ጋር በተያያዘ ተማሪን ማገድ
- ለመዝግየት ከተፈቀደው የመጨረሻ ጊዜ ከደረሱ በኋላ መዘግየቶችን እንደ ቀሪ መቁጠር

### ትምህርት ቤቶች የማይችሉት...

- የፕሪ-ኬጂ (pre-K) ተማሪዎችን ማገድ
- ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ ወይም ከቀሪ መዝገብ ላይ ማባረር
- ተማሪውን እንዲያጅብ ወላጅ መጥራት ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳው በሚያስፈልግበት ሰዓት ስብሰባው ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ
- ከ K-8 ድረስ አምስት ተከታታይ የትምህርት ቤት ቀናት ከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ፣ ከ 9-12 ድረስ አስር ተከታታይ የትምህርት ቤት ቀናት እገዳ
- በእገዳው ወቅት ተማሪው የትምህርት ሥራ እንዳይሰራ መከልከል ወይም ለክፍል ለማለፍ ወይም ለመመረቅ የሚያስፈልገውን ክሬዲት የማግኘት መብቱን መከልከል

### ኦሲ (OSSE)

- ስለ ትምህርት ቤት ከባቢ እና የፀባይ አስተዳደር መስክ ላይ ስላሉ ለውጦች ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA) መመሪያዎችን እና ግብዓቶችን ያቀርባል።
- ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች(LEA) እና ለትምህርት ቤቱ ሠራተኞች የሙያ ማሳደጊያ ዕድገቶችን ያቀርባል
- እያንዳንዱ የትምህርት ዓመት በሚጠናቀቅበት ጊዜ የግምገማ ትምህርት ቤት ሪፖርት ያቀርባል

### የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEA)

- የሥነ ስርዓት ማስከበር እርምጃዎችን በተመለከተ ለኦሲ (OSSE) ሪፖርት ያቀርባሉ
- በኦሲ (OSSE) የተቀመጡትን መስፈርቶችን የያዙ የትምህርት ቤት የሥነ ስርዓት ማስከበሪያ ፖሊሲዎችን ያወጣል
- ቀና የተማሪ ከባቢን ያጎለብታል

### ዲሲ ካውንስል

- የቀረቡ ምክሮችን ይገመግማል እና የሥነ ስርዓት ማስከበር ፖሊሲዎች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ ለውጦችን ያደርጋል
- ወጪን እና የገንዘብ ተጽእኖን ይቀጣጠራል

የማወቅመብት

# የትምህርት ክትትል

በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘትን በሚያስቡበት ወቅት የሚከተሉት ሊያስታውሷቸው የሚገቡ ጠቃሚ ነጥቦች ናቸው።

truancy: being absent from school without a permission or valid reason (unexcused absences)

**4**

After **four excused or unexcused absences**, the school MUST make a phone call home to discuss student's attendance.

**3**

After **three days of unexcused cumulative absences**, the school MUST send 3-day unexcused absence letter to parent or guardian.

**1**

After **one unexcused absence**, the school MUST make personal contact with the parent or guardian on the same day.

**7**

After **7 cumulative unexcused absences**, the school MUST send a MPD warning letter to the parent or guardian.

**5**

After **five cumulative unexcused absences**, the student is referred to Student Support Team (SST) for an attendance intervention conference.

**5**

After **five cumulative unexcused absences**, the school must send a 5-day unexcused absence letter to parent or guardian.

**20**

After **twenty consecutive unexcused absences**, the school must notify the parent or guardian that the student is eligible for withdrawal.

**15**

After **fifteen cumulative unexcused absences**, the school MUST submit referral to Court Social Services (CSS) within two days to for students aged 14-17.

**10**

After **ten cumulative unexcused absences**, the school MUST contact CFSA if the student is 13 years or younger, SST will notify school leader of action plan within two weeks.

A student is considered chronically truant after 10 days of cumulative unexcused absences.

For more information, visit https://osse.dc.gov/publication/attendance-and-truancy-resources-parents.

ውጤታማነትን

# ማርፈድ

የዲሲ የት/ቤት ትምህርት መጀመሪያ ጊዜዎች በት/ቤት እና በዓይነት ይለያያሉ፤ እናም ትክክለኛውን ጊዜ ለማወቅ የትምህርት ቤትዎን የመመሪያ መጽሀፍ ይመልከቱ።

ተማሪዎች እንደተገኙ ለመቆጠር በቀን ለ4 ሰዓት ከ 30 ደቂቃ መገኘት አለባቸው።

አንድ ተማሪ የሚያረፍድ ከሆነ ወይም የትምህርት ቀኑ 40% ካመለጠው፣ ቀኑን ሙሉ እንደቀረ ምልክት ይደረግበታል።



እያንዳንዱ LEA ምን ያህል ማርፈዶች ከአንድ ቀሪ ጋር እኩል እንደሚሆኑ ይወስናል።

ትምህርት ቤቶች ከ 20 ድምር ያለፈቃድ መቅረት በኋላ፣ ተማሪን ከምዝገባ ሊያስወጡ ይችላሉ።

ትምህርት ቤቶች ያለፈቃድ በመቅረት ወይም መዘግየት ምክንያት አንድን ተማሪ ሊያግዱ ወይም ሊያባርሩ አይችሉም።

* ከመኖሪያ ክልል ውጪ የሆኑ ወይም በሚመረጥ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ DCPS ተማሪዎች ከመጠን ባለፉ ማርፈዶች ምክንያት በድጋሚ እንዲመዘገቡ ላይጋበዙ ይችላሉ።

** የቻርተር ተማሪዎች ከመጠን ባለፉ ማርፈዶች ምክንያት በድጋሚ እንዲመዘገቡ ላይጋበዙ ይችላሉ።



ለተጨማሪ መረጃ፣ https://attendance.dc.govን ይጎብኙ

ውጤታማነትን

# የሚፈቀዱ መቅረቶች

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት እንደሚፈቀዱ መቅረቶች መቀበል ያለባቸው የትምህርት ቤት ቀሪዎች የሚከተሉት ናቸው፡

- ለተማሪው የሕክምና ወይም የጥርስ ቀጠሮዎች ፤ተማሪውን ያጋጠመ ሕመም ወይም ሌላ ተጨባጭ የጤንነት ችግር፤
- ከኮሎምብያ ዲስትሪክት ባለሥልጣናት በተሰጠው መመሪያ ምክንያት በተላላፊ በሽታ፣ ኢንፌክሽን፣ ወረርሽኝ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች ለህክምና ወይም በጤንነት ምክንያት ከሌሎች ተማሪዎች መለየት ስለሚያስፈልጋቸው የተገለሉ፤
- በተማሪ ቤተሰብ ውስጥ በተከሰተ የሞት አደጋ፤
- የሃይማኖታዊ በዓል ለመከታተል፤
- ለአንደኛ እና ለመካከለኛ ደረጃ ት / ቤት ተማሪዎች የትምህርት ቤት ጉብኝቶች (አንድ ቀን);
- ለ 2 ኛ ደረጃ ተማሪዎች የኮሌጅ ጉብኝቶች (እስከ 3 ድምር ቀናት);
- "ሴት ልጆቻችንን እና ልጆቻችንን ወደ ሥራ ቀን ይውሰዱ" ፤ተማሪው አሥራ ሰባት (17) ዓመት የሞላው ከሆነ፣ በትምህርት ቤቱ የተፈቀደ ቅጥር ወይም ሌላ የበጎ ፈቃደኝነት ሥራ ይህም በዚህ አንቀፅ ውስጥ የተገለጹ ማናቸውም የተፈቀዱ መቅረቶች በተማሪው አካዴሚያዊ አፈፃፀም ላይ ወይም በወቅቱ መመረቅ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እስከሌላቸው ነው።
- አንድ ተማሪ በድርጊቱ በመሳተፉ ወይም በፍርድ ቤት በመጠራቱ የፍርድ ቤት ወይም የአስተዳደር ችሎት ላይ መሳተፍ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤
- በትምህርት ቤት ባለሥልጣናት ህጋዊ በሆነ ሁኔታ ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም መወገድ፤
- በመጥፎ የአየር ሁኔታ፣ ኦፊሴላዊ እንቅስቃሴዎች፣ በዓላት፣ በመሳሪያዎች ብልሽት፣ አደገኛ ወይም ንጽሕና በጎደላቸው ሁኔታዎች፣ ወይም የትምህርት ቤት መዘጋት ወይም የትምህርት መቋረጥን የሚጠይቁ ሌሎች ሁኔታዎች ምክንያት ጊዜያዊ የተቋማት መዘጋት ወይም የትምህርት መቋረጥ፤
- የኮሎምብያ ዲስትሪክት ለተማሪ ማጓጓዣ ህጋዊ ኃላፊነት ባለበት ሁኔታ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መጓጓዣን ማቅረብ አለመቻል፣ የተማሪው የሕክምና ወይም የጥርስ ቀጠሮ ቀጠሮዎች፤
- ለወላጅ ተማሪዎች ወላጅ ህመም (ለ 5 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት ለቀረው ተማሪ የዶክተሩ ማስታወሻ ያስፈልጋል);
- በ LEA፣ ገለልተኛ፣ የግል ወይም ተጓዳኝ ትምህርት ቤት (ለወላጆች እና ለአሳዳጊዎች በተሰራጩ ፖሊሲዎች መሰረት) የጸደቁ አስቸኳይ ሁኔታዎች ወይም ሌሎች ሁኔታዎች።

**አንድ የትምህርት ተቋም፡**

1. በዚህ ዝርዝር ላይ ሊያክል ይችላል እንዲሁም
2. የቀረበውን ምክንያት ለማረጋገጥ የጽሁፍ መግለጫ ሊጠይቅ ይችላል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ https://attendance.dc.gov/ ን ይጎብኙ።

የማወቅመብት

# ምዝገባ

ራስዎን ይጠይቁ

የሚከተሉት ጥያቄዎች ምዝገባን በሚመለከቱበት ወቅት አጋዥ ውይይት መጀመርያ ናቸው።

መምህርዎን ይጠይቁ

- በመኖሪያ ክልሌ ያለውን ት/ቤት አውቃለሁ?
- ለመኖሪያ ክልል ትምህርት ቤቴ ተመዝግቤያለሁ?
- በመኖሪያ ክልሌ በሚገኘው ትምህርት ቤት ለመቀጠል እቅድ አለኝ?
- MySchoolDC.org ን ጎብኝቻለሁ ?
- መለያ (አካውንት) ፈጥሬያለሁ?
- የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የጋራ ሎተሪን የጊዜ ሰሌዳ አውቃለሁ?
- ለሎተሪው አመልክቻለሁ?
- በትምህርት ቤት ውስጥ ለኔ አስፈላጊው ምንድነው?(አካባቢ፣ ልዩ ፕሮግራሞች፣ ከትምህርት በፊት/በኋላ እንክብካቤ፣ ዩኒፎርም፣ ዓለም አቀፍ ባካሎሬት ሁለት ቋንቋን ማጥናት)
- በምዝገባ ሂደቱ ላይ ያልተገነዘብኩት ነገር አለ?
- መጠየቅ እያለብኝ መጠየቅ ያልያዝኩት ነገር ምንድነው?

- የ DCPS ትምህርት ቤት ወይም ቻርተር ትምህርት ቤት ናችሁ?
- ለምዝገባ ምርጫዎችን ታቀርባላችሁ? ከሆነ፣ ምንድናቸው?
- በ MySchoolDC.org ላይ ያለው መረጃችሁ ትክክለኛ/ወቅታዊ ነው?
- በሎተሪ ውስጥ ትሳተፋላችሁ? ካልሆነ፣ እንዴት ማመልከት እችላለሁ?
- የተማሪ መመሪያችሁን በመስመር ላይ ማግኘት እችላለሁ? ተማሪዬን ከማስመዘገቤ በፊት በዚሁ ላይ ለመወያየት ከአንድ ሰው ጋር መቀመጥ እችላለሁ?
- ቤተሰቦች የመሆን እድል ላላቸው ማስተናገጃ ክፍት ክፍሎች አላችሁ? ሰራተኞቹን ለማየት እና ሥርዓተ ትምህርቱን ለመገምገም ተጨማሪ መንገዶች አሉኝ?
- መጠየቅ እያለብኝ መጠየቅ ያልያዝኩት ነገር ምንድነው?

ስለ ትምህርት ቤቶች/ምዝገባ፣ የበለጠ መረጃ ለማግኘት https://myschooldc.org ን ይጎብኙ።
ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ስላሉት ዕድሎች መረጃ ለማግኘት https://learn24.dc.gov ን ይጎብኙ።

ውጤታማነትን

# Pre-K3 እና Pre-K4

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ነገሮች

### ትራንዚት

በዲሲ ያሉ ተማሪዎች የሕዝብ ትራንስፖርት በነፃ ይጠቀማሉ፣ መጓጓዣው በትምህርት ቤቱ የሚቀርበው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች አካል ብቻ በመሆን ነው።

### ልዩ ትምህርት ቤቶች

Montessori እና Reggio Emilia ተማሪዎች ይበልጥ በነፃነት እና በተናጠል ሲማሩ በመደገፍ ላይ የሚያተኩር የመማር ዘዴን ይጠቀማሉ። አብዛኛዎቹ የ Montessori አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪው በ Montessori ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት መከታተልን ይጠይቃሉ።

### ከትምህርት ሰዓት በፊት/በኋላ እንክብካቤ

ጥቂት ት/ቤቶች ወላጆች ተማሪዎቻቸውን በጊዜ እንዲያስቀምጡ ወይም ተማሪዎችን ከመለቀቂያ ሰዓት በኋላ እንዲወስዱ ይፈቅዳሉ።

### መጋቢ ትምህርት ቤቶች

እያንዳንዱ የ DCPS አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎቹ እንዲሳተፉ በቀጥታ የሚጋበዙበት የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አለው። አንዳንድ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ጥምረት/ስምምነት አላቸው።

### ቋንቋ

አንዲንድ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከእንግሊዝኛ ውጪ የሆነ ቋንቋ እንደ ፕሮግራም ወይም የትምህርት አማራጭ ያቀርባሉ።

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ነገሮች፡

### ቻርተር ት/ቤቶች

እያንዳንዱ ቻርተር ትምህርት ቤት ለ pre-K3 እና ለ pre-K4 የራሱን ስርዓተ ትምህርት ያዳብራል። አንዳንድ ቻርተሮች የፌደራሉን Head Start Early Learning Outcomes Framework (የቅድሚያ ጅማሮ የቅድመ-ትምህርት የውጤቶች መዋቅርን) ይጠቀማሉ።

### DCPS

DCPS ስርዓተ ትምህርቱን እና የተማሪ/መምህር ጥምርታ መስፈርቶችን የሚያወጣውን የፌደራሉን የቅድመ ጅማሮ የቅድመ ትምህርት የውጤቶች መዋቅርን ይጠቀማል።

### የደንብ ልብሶች

ሁሉም የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የደንብ ልብስ እንዲለብሱ አይጠይቁም። ዩኒፎርም የሚጠይቅ ትምህርት ቤት አንድ ተማሪ ያለዩኒፎርም ት/ቤት እንዲከታተል አይፈቅድም።

### ማህበረሰብ-ተኮር ድርጅቶች

DCPS ያልሆኑ ወይም በቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪዎች ስርዓተ ትምህርቱን እና የተማሪ/መምህር ጥምርታ መስፈርቶችን የሚያወጣውን የ OSSE የቅድመ ትምህርት ደረጃዎችን ይጠቀማሉ።

ለበለጠ መረጃ፣ https://osse.dc.gov/service/early-learning-services-parents-pre-kindergarten-services ን ይጎብኙ ወይም http://www.myschooldc.org/ ።

ውጤታማነትን

# ቤት አልባነት

የሚከተሉት ቤት አልባነት በሚገጥምበት ወቅት አጋዥ ውይይት መጀመሪያ ናቸው።

የ McKinney-Vento Homeless Assistance Act (የቤት አልባዎች መርጃ ሕግ) የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን በማሰስ ሂደት ውስጥ ለቤት አልባ ቤተሰቦች ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል የፌዴራል ሕግ ነው።

## "ቤት አልባ ተማሪዎች" የሚከተሉትን ተማሪዎች ያካትታል፡

- ቋሚ፣ መደበኛ እና በቂ የማታ መኖሪያ የሌላቸውን፤
- በቤት ማጣት፣ በኢኮኖሚ ችግር ወይም ተመሳሳይ ምክንያት የሌሎች ሰዎችን መኖሪያ የሚጋሩ፤
- የተገቢ የመጠለያ አማራጭ ባለመኖሩ በሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ በተሳቢ ፓርኮች ወይም በካምፕ ወለሎች ውስጥ የሚኖሩ፤
- በድንገተኛ ሁኔታ ወይም በመሸጋገሪያ መጠለያዎች የሚኖሩ (የዲሲ የሽግግር መኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ)፤
- በሆስፒታሎች ተትተው ወይም የማደጎ ቦታ ምደባን በመጠባበቅ ላይ ያሉ፤
- ለሰብዓዊ ፍጡር የመኝታ ቦታነት ባልተገነባ ወይም በመደበኛነት ለሰዎች መኖሪያነት ጥቅም ላይ የማይውል ቀዳሚ የምሽት መኖሪያ ያላቸው፤
- በወላጅ ወይም በአሳዳጊ አካላዊ ቁጥጥር ስር ያልሆኑ እና ከላይ ያሉትን ማናቸውም ሁኔታዎች የሚያሟሉ፤ ወይም
- ከዚህ በላይ በተገለጹት ሁኔታዎች ውስጥ የሚኖሩ የሚፈልሱ ልጆች ናቸው

## የተማሪው/ዋን የተሻለ ጥቅም መሰረት በማድረግ፣ LEA ...

- ተማሪው አስፈላጊውን ክትባት፣ የሕክምና መዛግብት፣ ዩኒፎርም ወይም ሌሎች ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንዲያገኝ ማገዝ ይኖርበታል።
- የተማሪውን ትምህርት አሁን ተማሪው ባለበት ትምህርት ቤት መቀጠል።
- በአሁኑ ጊዜ በት/ቤት ካልተመዘገበ፣ ተማሪውን በአካባቢው ትምህርት ቤት በአስቸኳይ ማስመዝገብ።
- ተማሪው ለመመዝገብ በመደበኛነት አስፈላጊ የሆኑትን ሰነዶች ማዘጋጀት ባይችልም እንኳ ቤት አልባውን ተማሪ ወዲያውኑ መመዝገብ።

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሁሉም የመኖሪያ ቤት የሌላቸው ልጆች እና ወጣቶች ሙሉ ለሙሉ ብቁ እና ፍላጎት ላላቸው የትምህርት ፕሮግራሞች በሙሉ ለመሳተፍ እንደሚችሉ ያረጋግጣል።

ለበለጠ መረጃ https://osse.dc.gov/service/education-homeless-children-and-youth-program ን ይጎብኙ።

ኦፊስኦፍ ስቱደንት አድቮኬት
(የተማሪ ተሟጋች ጽህፈት ቤት)

# ቤት-አልባነት

## የመገልገያቁሳቁስ

### ሰነዶች

ቤት-አልባልጆች ሙሉ ሰነዶች ሳያቀርቡ መመዝገብ ይፈቀድላቸዋል። የመኖሪያማረጋገጫ የሌላቸው ወይም የክትባት ማረጋገጫ የሌላቸው ቤተሰቦች ተማሪዎቻቸው ማስመዝገብ ይችላሉ።

### ትራንስፖርቴሽን

ትምህርት ቤቶች ለቤት-አልባ ተማሪዎች ትራንስፖርቴሽን ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ይህም ለተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የሚያደርስና የሚመልስ የሜትሮ ፈር ማቅረብ ያጠቃልላል። ታናናሽ ልጆች ያላቸው ወላጆችም ተማሪዎቻቸው ወደ ትምህርት ቤት ለመውሰድ ሜትሮ ፈር መቀበል ይችላሉ።

### ዩኒፎርሞች

ቤት-አልባተማሪዎች ከትምህርት ቤታቸው ነጻ ዩኒፎርሞች ማግኘት ይችላሉ። አንዳንድትምህርት ቤቶች ማጠቢያና ማድረቅያ ማሽኖች እንዲጠቀሙ ይፈቅዳሉ። ትምህርትቤትዎ ምን እንደሚያቀርብ ለማወቅ ለአማካሪዎ (ካውንስለር) ያነጋግሩ።

### ሀብቶች

እያንዳንዱትምህርት ቤት የቤት-አልባ ሊያይዘን አለው። ቤት-አልባሊያይዘኖች ቤት-አልባ ልጆችን ለትምህርት ቤት አቅርቦቶች፣ ክትባቶች፣ እና የኤስ.ኤ.ቲ./ኤ.ሲ.ቲ./ጂ.ኢ.ዲ. ፈተናዎች ክፍያዎች በመክፈል ረገድ ሊረዱ ይችላሉ። ምክር (ካውንስሊንግ)፣ አስጠኚ፣ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት በመፈለግ ወይም በመክፈል ረገድ እርዳታ የሚፈልጉ ቤት-አልባቤተሰቦች ለትምህርት ቤታቸው ቤት-አልባ ሊያይዘን ማነጋገር ይኖርባቸዋል። የእርስዎማን እንደሆነ እንዲነገርዎ ፕሪንሲፓልዎን(ዳይሬክተርዎን) ወይም የሚወዱት አስተማሪን ይጠይቁ። ትምህርት ቤቶች እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች ለመርዳት የሚሆንተጨማሪ ገንዘብ ሊኖራቸው ይችላል

### "ቤት-አልባ" ማለትምንማለትነው?

ተማሪዎችቋሚና ተገቢ የሆነ በሌሊት የሚተኙበት ቦታ የሌላቸው ከሆነ እንደ ቤት-አልባ ተደርገው ይቆጠራሉ። ይህከጓደኞች ወይም ቤተሰቦች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ መቆየት፣ በመጠለያ መተኛት፣ ወይም በጊዝያዊ የመኖሪያ ቤት ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ ያካትታሉ።

### ኤጀንሲዎች

#### ለወጣቶች ተስማሚ የሆኑ ኤጀንሲዎች

**Sasha Bruce Youthwork**
ድንገተኛ:
(202) 547-7777
መረጃ:
(202) 675-9340

**Covenant House**
(202) 610-9600

**Latin American Youth Center**
(202) 695-1278

**SMYAL**
(202) 546🌈940

**Wanda Alston House**
(202) 733-3643

**Re-Engagement Center** 🌈
(202) 671-2539

**Homeless Children's Playtime Project**
(202) 329-4481

#### ተጨማሪ ኤጀንሲዎች

**DC Coalition for the Homeless**
(202) 347-8870

**DCPS Homeless Children and Youth Services**
(202) 724- 1338

**Bread for the City**
NW : (202) 265-2400
SE : (202) 561-8587

**Calvary Women's Shelter**
(202) 678-2341

**Community of Hope**
(202) 526-0017

**Catholic Charities**
(202) 772-4300

**Washington Legal Clinic for the Homeless**
(202) 328-5500

**Friendship Place**
(202) 364-1419

**Miriam's Kitchen**
(202) 452-8926

**OSSE Homeless Education Program**
(202) 727-6436

**So Others Might Eat (SOME)**
(202) 797-8806

**Thrive DC**
(202) 737-9311

**Housing Up**
(202) 291-5535

**Virginia Williams Family Resource Center**
(202) 526-0017

የማወቅመብት

# የወታደር ቤተሰቦች

በንቁየውትድርና አገልግሎት ያለ ወላጅ ያላቸውና በዲ.ሲ. ድንበሮች ውስጥ በውትድርና ቦታዎች የሚኖሩ ወላጆች ያላቸው ከቅድመ-ኪንደርጋርተን-12የሆኑ ተማሪዎች በትምህርት ቤት አመቱ በማንኛውም ጊዜ፣ የትምህርት ክፍሉ እና/ወይም ፕሮግራሙ ክፍት ቦታ እስካለ ድረስ፣ በመረጡት የዲ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ቤት መመዝገብ ይችላሉ።

### ትራንስፖርቴሽን?

ለሁሉምትምህርት ቤቶች የማይገኝ ቢሆንም፣ የዲፓርትመንት ኦፍ ዲፌንስ (መከላከያ ሚኒስቴር) በጀይ.ቢ.ኤ.ቢ.ለሚኖሩ ቤተሰቦች ትራንስፖርቴሽን ያቀርባል። ለተጨማሪመረጃ የጀይ.ቢ.ኤ.ቢ.የትምህርት ቤት ሊያይዘን ኦፊሰር ወይም የጀይ.ቢ.ኤ.ቢ.የትምህርት ቤት አውቶቡስ አስተባባሪን ያነጋግሩ።

### ሙቪንግፖስት ሎተሪ?

ቤተሰቦች በፖስት ሎተሪ ጊዜ ማይስኩልዲ.ሲ.መተግበሪያ በመጠቀም ማመልከት ይችላሉ። ተማሪዎችየመሳተፍ መብት ባላቸው ትምህርት ቤት የተረጋገጠ ቦታ አላቸው፣ ሌሎች አማራጮች መጠቀም የሚችሉት ግን አማራጮቹ ያሉ ከሆነ ብቻ ነው።

### የመኖሪያቤት ትእዛዞች የሉም (ኖ ሀውዚንግ ኦርደርስ)?

የመኖሪያቤት ትእዛዞች የሌላቸው ቤተሰቦች ቢሆኑም በማይስኩልዲ.ሲ.የሎተሪ ሂደት መሳተፍ ይችላሉ። ሂደቱበተመለከተ መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤቱ ሊያይዘን ኦፊሰርን ያነጋግሩ።

### የጣቢያለውጥ (ቸንጅ ኦፍ ስቴሽን)?

በዚህጊዜ የመጨረሻ ውሳኔ የማድረግ መብት ያለው ትምህርት ቤቱ ነው። ቤተሰቦች የጣቢያለውጥ ለማድረጋቸው በፊት ትምህርት ቤቱን ወዲያውኑ በማግኘት ሁኔታውን እንዲያብራሩ ይበረታታሉ።

### ትምህርትቤቶችን ማስተላለፍ (ትራንስፈሪንግ ስኩልስ)?

በግማሽአመት በዲ.ሲ. ትምህርት ቤቶች መካከል መተላለፍ ለማድረግ ማመልከቻ ማስገባት ይቻላል፣ ነገር ግን በርግጠኝነት ይሳካል ማለት አይደለም። ስለርስዎየተለየ ሁኔታ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ማይስኩልዲ.ሲ.የ24 ሰአታት አገልግሎት ዘንድ ይደውሉ።

### የመሳተፍመብት?

የልጅዎየመሳተፍ መብትለማወቅ፣ድንበር-ውስጥ ወንበር በርገጥኘት የሚያገኙበት ትምህርት ቤት ለማወቅ የማይስኩልዲ.ሲ.ድረገጽ ይጎብኙና ትምህርት ቤት ፈላጊ መሳሪያን (ስኩል ፋይንደር ቱል) ይጠቀሙ።

**ጀይ.ቢ.ኤ.ቢ.የትምህርት ቤት ሊያይዘን ኦፊሰር፡** (202) 404-1014
**ጀይ.ቢ.ኤ.ቢ.የትምህርትቤት አስተባባሪ፡** (202) 767-8138
**ማይስኩልዲ.ሲ.የ24 ሰአት የስልክ መስመር፡** 202-888-6336

ውጤታማነትን

# የልዩ ፍላጎት ትምህርት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን በሚመለከቱበት ወቅት አጋዥ ውይይት መጀመርያ ናቸው።

## ራስዎን ይጠይቁ

- ተማሪዬ ለግለሰባዊ የትምህርት እቅድ ብቁ ሊሆን የሚያስችለው አካለ
- ትምህርት ቤቱ ልጄን አካል ጉዳተኝነትን እንዲገመግመው ጠይቄያለሁ?
- ጥያቄው በቃል ነበር ወይስ በጽሁፍ?
- ለልጄ ግምገማ የጠየቅኩበት ሰነድ አለኝ?
- የሁሉም ስብሰባዎች ቀናት በሙሉ አሉኝ? ለመሳተፍ ተዘጋጅቻለሁ?
- በስብሰባው ውስጥ ተከራካሪ እንዲገኝ እፈልጋለሁ?
- የተቀበልኳቸውን የወረቀት ስራዎች ሁሉ አንብቤ ግልባጭ አስቀምጫለሁ/ ወይም ፈርሚያለሁ?
- ሁሉንም የተጠየቀውን መረጃ ለትምህርት ቤቱ አቅርቤያለሁ?
- Aትምህርት ቤቱ የተማሪዬን የአካል ጉዳት ማስተናገድ ካልቻለ ለተማሪዬ ትምህርት ቤት ሊለወጥ እንደሚችል አውቃለሁ?
- መጠየቅ እያለብኝ መጠየቅ ያልያዝኩት ነገር ምንድነው?

## መምህርዎን ይጠይቁ

- ተማሪያዬ የተጠናከረ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ለመወሰን ቀደም ብሎ የሰበሰባችሁት መረጃ ምንድነው?
- ልጄ የመማር ችሎታው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያሳድር የአካል ጉዳት ላይ እንዲገመገም መጠየቄን ተረድተዋል?
- ጥያቄዬን በሰነድ መዝግባችሁ አስቀምጣችኋል?
- ቀጥሎ ምን ልጠብቅ እችላለሁ?
- ይህን ሂደት በተመለከተ ጥያቄ ካለኝ ማንን ማነጋገር እችላለሁ ማንስ ያናግረኛል?
- በእውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ፣ የቅድሚያ በጽሑፍ የቀረበ የምዘና ማሳሰቢያ እና የአካሄድ መከላከያዎችን ማግኘት የምችልበት ምክንያታዊ ጊዜ ምን ያህል ነው ?
- ከኔ የምትፈልጉት ተጨማሪ መረጃ አለ?
- በዚህ አካባቢ ውስጥ ለመቀበል የማትችሉት የአካል ጉዳቶች አሉ?
- መጠየቅ እያለብኝ መጠየቅ ያልያዝኩት ነገር ምንድነው?

ለበለጠ መረጃ፣ https://studentadvocate.dc.gov/node/11539322 ን ይጎብኙ።

# የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሕግ አጠቃላይ እይታ

## ሶስት የፌደራል ሕጎች የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች መብቶችን ያረጋግጣሉ፦

1. Americans with Disabilities Act (ADA፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካውያን ሕግ)


2. Section 504 of the Rehabilitation Act ("Section 504፣ የመልሶ ማቋቋሚያው ሕግ ክፍል 504) → እነዚህ የ 504 እቅድ ይቀበላሉ።

3. Individuals with Disabilities Education Act ("IDEA"፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ) → እነዚህ ልጆች የ IEP እቅድ ይቀበላሉ።

# Section 504 & IDEA

## በጨረፍ ታ

### ለ Section 504 እና IDEA ብቁነት




Section 504 – ዋና ዋና የህይወት ተግባራትን የሚገድቡ የአካል ወይም የአእምሮ ችግር ያለባቸው ነገር ግን ለ IEP ብቁ ለመሆን የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች የማያሟሉ።

IDEA – የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚፈልጉ ተብለው በ IDEA እውቅና ከተሰጣቸው ከ 13ቱ የአካል ጉዳት ምድቦች ውስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች።

# በዲሲ ያለው ሕግ እና ገጽታ

በግምት
14%

የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች (ብሄራዊ አማካይ 13%)

በግምት.
8,000

በተለመዱ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ያሉ የልዩ ፍልጎት ትምህርት ተማሪዎች

በግምት.
5,000

በዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ያሉ የልዩ ፍልጎት ትምህርት ተማሪዎች

የመማር ስን ክልና

በጣም የተለመደ የስንክልና አይነት

ማካተት

በልዩ ፍላጎት ትምህርት ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አብዛኛውን የቀን ውሎዋቸውን በመደበኛ የትምህርት ክፍሎች ያሳልፋሉ

በ 2014፣ የዲሲ ምክር ቤት የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ያሻሻለ የህግ ጥቅል አውጥቷል። ሕጉ የሚያካትተው:Special Education Student Rights Act (የልዩ ፍላጎት ትምህርት የተማሪ መብቶች ሕግ)፣ Enhanced Special Education Services Act (የተሻሻለው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ሕግ) እና Special Education Quality Improvement Act (የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ሕግ) ነው።

## 1 የልዩ ፍላጎት ትምህርት የተማሪ መብቶች ሕግ

- ስብሰባ ከመደረጉ 5 የሥራ ቀናት አስቀድሞ የግምገማና የረቂቅ IEP ቅጂዎችን የማግኘት መብት
- ልጁን በወቅቱ ምደባ ውስጥ እና በተጠቆመ ምደባ ውስጥ የመመልከት መብት (በወላጆች ምትክ አንድ ሌላ ሰው ሊያደርገውም ይችላል)
- ከስብሰባ በኋላ በ 5 የሥራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ IEP ቅጂዎችን የማግኘት መብት

## 2 የተሻሻለው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ሕግ

- ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ግምገማ የተጠቆሙ ልጆች የወላጅ ፈቃድ በተሰጠ በ 60 ቀናት ውስጥ ወይም ከተጠቆሙ በ 90 ቀናት ውስጥ መገምገም አለባቸው

## 3 (የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ሕግ

ይበልጥ ውጤታማ ለሆኑ የልዩ ትምህርት መርሃ ግብሮች ግልጽ የሆኑ ሀላፊነቶችን እና የተሻሉ ቁጥጥሮችን ለማቅረብ የተነደፈ ነው

# 504 ዕቅድ ወይም IEP

## ምንድነው?

የ 504 ዕቅድ ለአንድ የአካል ጉዳት ወይም እክል ያለበት ልጅ "ነፃ ተስማሚ የሕዝብ ትምህርት" እንዴት እንደሚሰጥ እና እቅድ እንደሌላቸው እኩዮቻቸው ለትምህርት አቅርቦቱ ተመሳሳይ ተደራሽነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ነው።

IEP (ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም) አንድ ብቁ የሚያደርግ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ ትርጉም ያለው የትምህርት እድገት ሊያገኝ የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ "ነፃና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት" እንዴት እንደሚሰጥ የሚያሳይ ዕቅድ ነው።

# 504 ዕቅድ ወይም IEP

## በፕሮግራሙ/ዕቅዱ ውስጥ ምንድነው ያለው?

**የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡**

- የተወሰኑ ማመቻቸቶች፣ ድጋፎች ወይም አገልግሎቶች
- አገልግሎቶቹን የሚያቀርቡት ስም
- ዕቅዱን በሥራ ላይ ለማዋል ኃላፊነት ያለባቸው ግለሰቦች ስም

***504 ፕላኖች እንደሁኔታው ተለዋዋጭ ናቸው፣ ማለትም IEP የሚያካትታቸውን በርካታ ነገሮች ሊያካትት ይችላል፤ ነገር ግን፣ ይህ ተለዋዋጭነት ማለት ት/ቤቱ ምን እቅድ ውስጥ ማካተት እንዳለበት ለመወሰን (ከወላጅ ግቤት ጋር) የመገመት ስልጣን አለው ማለት ነው።

**የሚከተሉትን የግድ ማካተት አለበት፡**

- የልጁን ወቅታዊ የአካዳሚክ እና ተግባራዊ የአፈፃፀም ደረጃዎች
- ዓመታዊ የትምህርት ግቦች እና እንዴት ክትትል እንደሚደረግባቸው
- ልጁ የሚቀበላቸውን አገልግሎቶች
- የአገልግሎቶች የጊዜ ሰሌዳ (መቼ፣ ለምን ያህል ጊዜ፣ በየምን ያህል ጊዜው)
- ማመቻቸቶች (በመማሪያ ከባቢውላይ የሚደረጉ ለውጦች)
- ማሻሻያዎች (ልጁ እንዲያውቃቸው የሚጠበቁ ነገሮች ላይ ያሉ ለውጦች)
- በመደበኛ ትምህርት የሚጠፋው ጊዜ እና በልዩ ፍላጎት የትምህርት ክፍሎች የሚጠፋው

# ልጅ አፋላጊ

ልጅ አፋልጊ (Child Find) የአካለ ስንኩልነት ያለባቸው እና ልዩ ትምህርት እና ተዛመጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልጋቸው ሁሉም ልጆች መለየታቸውን፣ መገኘታቸውን እና መመርመራቸውን የሚያረጋግጥ ሂደት ነው።

በልጁ/ጅቷ ዕድሜ መሰረት ሃላፊነቱ በተለያዩ ኤጀንሲዎች ላይ ይወዳቃል፥

| ዕድሜ/የክፍል ደረጃ | ሃላፊነት ያለበት ኤጀንሲ |
|---|---|
| ከውልደት እስከ 2 1/2 ዓመት ከሆነ | ኦሲ (OSSE):ስትሮንግ ስትራት (Strong Start) |
| ከ 2 1/2 ዓመት እስከ መዋዕለ ሕፃናት ኪንደርጋርተን ድረስ | የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ት/ቤቶች (DCPS Early Stages) ወይምየቻርተር ቅድመ መዋዕለ ሕፃናት አገልግሎት ሰጪዎች (charter PK providers) |
| ከ1ኛ ክፍል እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) እና የግል ትምህርት ቤቶች (አስፈላጊ ከሆነ ከኦሲ (OSSE) ድጋፍ በማግኘት) |

# የመመሪያ ጥበቃዎች

አይዲያ (IDEA) የነፃ ኣና ተገቢ የሕዝብ ትምህርት [[ፌፐ( FAPE)] ክለከላ አለ ተብሎ የሚያምን ከሆነ ለወላጆች መጠነ ሰፊ የመመሪያ ጥበቃዎችን ይሰጣል:

- መደበኛ መድሐኒት አሰጣጥ
- የግዛት ቅሬታ
- የፍትህ ሂደት ቅሬታ

እንደ ትምህርት ቤቱ ኤጀንሲ፣ የግዛቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ [[ Office of the State Superintendent of Education (OSSE)] የቅሬታ አፈታት ቢሮ (Office of Dispute Resolution) ትምህርት ቤቶች የፌደራል እና የአካባቢውን ልዩ ትምህርት ሕግ እንዳይተላለፉ ያግዛል።ወላጆች የነፃ ኣና ተገቢ የሕዝብ ትምህርት [[ፌፐ( FAPE)] ክለከላን እንዲጣራ ከኦሲ ( OSSE) ጋር ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

**የኦሲ የግዛቱ ቅሬታ ቢሮ (OSSE State Complaints Office)**
202-742-7860
https://osse.dc.gov/service/specialized-education-state-complaints

**ኦሲ የቅሬታ አፈታት ቢሮ (OSSE Office of Dispute Resolution)**
202-698-3819
https://osse.dc.gov/service/office-dispute-resolution-odr

ውጤታማነትን

# የጣልቃገብነት ምላሽ

የሚከተሉት ትምህርታዊ ወይም ባህርያዊ ጣልቃ ገብነትን በሚመለከቱበት ወቅት አጋዥ ውይይት መጀመሪያ ናቸው።

የጣልቃ-ገብነት ምላሽ (RTI) በክህሎት ወይም ትምህርት እየተቸገሩ ያሉ ተማሪዎችን ለመርዳት አስተማሪዎች የሚጠቀሙበት ሂደት ነው፤ እያንዳንዱ መምህር ከማንኛውም ተማሪዎች ጋር በክፍል ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማገዝ ጣልቃ-ገብነትን (የማስተማር አካሄዶች ስብስብን) ይጠቀማል—ልዩ ፍላጎት ላላቸው ወይም ለመማር እክል ላለባቸው ልጆች ብቻ አይደለም።*

* https://www.specialeducationguide.com/pre-k-12/response-to-intervention/

- በ Response to Intervention (RTI፣ የጣልቃ-ገብነት ምላሽ) ቡድን ውስጥ ያለው ማነው?
- ተማሪን ወደ RTI የሚመራው ማነው?
- RTI ማለት ለልዩ ፍላጎት ትምህርት በልጄ ላይ ክትትል እየተደረገ ነው ማለት ነው?
- የ RTI ሂደቱ ለምን ያህል ጊዜ ነው? ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ግምገማ ከመጠየቄ በፊት ልጄ የ RTI ሂደቱን ማጠናቀቅ አለበት ማለት ነው?
- የተማሪዬን ስኬት ለማረጋገጥ የጀመራችሁት ምን ዓይነት ጣልቃ-ገብነት ነው?
- መቼ ነው RTI የሚጀምረው? በ RTI ሂደት ውስጥ ስላሉ ለውጦች በየ ምን ያህል ጊዜው መረጃ ይደርሰኛል?
- በ RTI ሂደት ወቅት ምን አይነት የማስተማር ጣልቃ ገብ እርምጃዎች ይቀርባሉ? በ RTI ሂደት ወቅት ምን ዓይነት የመልካም ባህሪይ ድጋፎች ይቀርባሉ?
- የጣልቃ-ገብነት ስኬቶችን እንዴት ትከታተላላችሁ? የተማሪዬን መሻሻል በየ ምን ያህል ጊዜው ትለካላችሁ?
- የ RTI ስብሰባዎች መቼ ነው የሚካሄዱት?መገኘት እችላለሁ? ስለ ግኝቶቹ በየ ምን ያህል ጊዜው ታሳውቁኛላችሁ?
- መጠየቅ እያለብኝ መጠየቅ ያልያዝኩት ነገር ምንድነው?





ለተጨማሪ መረጃ፣ https://studentadvocate.dc.gov/node/1153932 ን ይጎብኙ።

# የመስመር ላይ ድጋፍ

## የማኅበረሰብ ሀብት መመሪያ

በድር ጣቢያችን ላይ በ 20 የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የተመደቡ ከ 400 መርጃዎችን ከአጠቃላይ የመርጃ ኃብቶች መመሪያ ጋር እናስተናግዳለን። ይበልጥ ለተሟላ አጠቃላይ የመርጃ ሀብቶች እና ድጋፎች ዝርዝር እባክዎን ድረገፃችንን https://studentadvocate.dc.gov ይጎብኙ።

## የመገልገያ መሳሪያዎች

**Head to**

studentadvocate.dc.gov

**Click**

ላይ ጠቅ ያድርጉ

**Explore**

(የመርጃ መሳሪያዎቻችን)

- የመከራከሪያ እና የማግባቢያ መርጃዎች ስብስብ
- ትምህርት ክትትል እና መፎረፍ (ወላጅ እና ት/ቤቱ ሳያውቁ ከትምህርት መቅረት
- የባህሪ እና የአዕምሮ ጤንነት
- የዲስትሪክት የአስተዳደር መዋቅር
- ውጤታማ ግንኙነት
- ውጤታማ ግንኙነት)
- የምረቃ ቅድመ መስፈርቶች
- ቤት አልባነት
- የወላጅ አመራር መርጃዎች ስብስብ
- ማወቅ ያለብዎን መጠየቂያ ሉሆች
- አስተማማኝ መተላለፊያ
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ሌሎችየትምህርት ቤት ድጋፎች
- የተማሪ አመራር
- ፈተናዎች እና ምዘናዎች

* This Parent & Family Go-To Guide is also available online.

## ማወቅ የሚገቡ ቁጥሮች

ኦፊስ ኦፍ ዘ ስቴት ሱፐርኢንቴንደንት ኦፍ ኢጁኬሽን........................................ (202) 727-6436
OSSE Division of Transportation Parent Resource ቸንተር........................................ (202) 576-5000
ለሕዝብ ትምህርት የእንባ ጠባቂ ቢሮ.............................................................. (202) 741-0886
የ DCPS አቤቱታ.................................................................................................... (202) 442-5405
My School DC...................................................................................................... (202) 888-6336
የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ.............................................................. (202) 328-2660
የትምህርት ምክትል ከንቲባ.......................................................................... (202) 727-3636

## ለድንገተኛ እርዳታ ጥሪ ሊያደርጉልን ይፈልጋሉ?

የእርዳታ መጠየቂያ መስመራችን (RFA) ከሰኞ እስከ ዓርብ 9 am -5 pm ይሠራል። ሰራተኞቻችን በቀጥታ መልስ የሚሰጡ ሲሆን ስለ ተማሪዎ ጉዳይ ወይም በዲስትሪክቱ ስላለው የሕዝብ ትምህርት በተመለከተ ላለዎት ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች መልስ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።

**የ RFA መስመር፡: 202.741.4692**

The Office of the Student Advocate was established by the Council of the District of Columbia through the Parent and Student Empowerment Act of 2013 . The office provides guidance and resource supports for families in order to assist them in navigating our complex system of public education in DC.

For more information, visit studentadvocate.dc.gov.

The Office of the Student Advocate is an independent office housed within the DC State Board of Education.